የሰ.መ.ቁ 235053

ቀን መጋቢት 29 2015ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካቾች፡ 1ኛ. ወ/ሮ እቴነሽ ቶሎሳ ቡልቻ

2ኛ. አቶ ስለሺ ቶሎሳ ቡልቻ

3ኛ. አቶ ፈለቀ ቶሎሳ ቡልቻ

4ኛ. ወ/ት ቤተልሄም ቶሎሳ ቡልቻ

} ጠ ሀይለሚካኤልል ቀረቡ (1ኛ አመልካችም ጭምር)

ተጠሪ፡ ካራ ቆሬ ሪል ስቴት ኃ/የተ/የግ/ማህበር - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካቾች የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 131795 በ7/10/14ዓ.ም በሰጠው ብይን እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 294480 በ27/12/14ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ቅር በመሰኘት በ25/1/15ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካቾች በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ የአመልካቾች አባት አቶ ቶሎሳ ቡልቻ በዳኜ ይዞታውና አካባቢው ወደ አዲስ አበባ ከተማ ከመካለሉ በፊት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ግብር እየከፈሉ ለእርሻ የሚጠቀሙበት ይዞታ በቀድሞ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 በአሁኑ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 10 ልዩ ስሙ 72 ቀጠና አዋሳኞቹ በክሱ የተጠቀሱ የቦታ ስፋቱ 1639.30ካ.ሜ በሆነው ላይ ሁለት ቤቶችን ሰርተው ሲኖሩ በ20/8/99ዓ.ም በመሞታቸው አመልካቾች የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች

መሆናችንን በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በተሰጠ ውሳኔ አረጋግጠን፤ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ አመልካቾች ከላይ የተጠቀሰው ሀብት የጋራ ባለቤቶች መሆናችን ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች በድርሻችን መሰረት የንብረቱ ባለቤትነት ካርታ እንዲሰጠን ለክ/ከተማው የይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት ጥያቄ አቅርበን ከሌሎች ከወረዳ 10 አስተዳደር ለካርታ ወደ ክ/ከተማው የተላኩትን አርሶአደሮችን መረጃ የወረዳው አመራሮችና የአርሶአደሮች ተወካይ ኮሚቴዎች በቦታው በአካል ተገኝተው በ15/8/11ዓ.ም በተጻፈ ቃለጉባኤ አመልካቾች ካሳ እና ምትክ ቦታ ያልወሰዱ መሆኑን እንዲሁም የቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 አስተዳደር በ9/3/12ዓ.ም ለክ/ከተማ የመሬት ልማትና ማደስ ጽ/ቤት የአመልካቾችን መረጃ አጣርቶ በላከው ደብዳቤ ተጠቃሹ ቦታ የአርሶአደር አቶ ቶሎሳ ቡልቻ በዳኔ እና የልጆቹ የአመልካቾች መሆኑን በቦታው ላይ ሁለት ቤቶች መኖራቸውን፤ አመልካቾች አጥረው እየኖሩበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ከላይ በተገለጸው የአመልካቾች ንብረት ላይ ተጠሪ ተገቢ ባልሆነ መንገድ በ27/1/12ዓ.ም የተሰጠ የመዝገብ ቁጥር እና አዋሳኞቹ ያልተጻፉበት ካርታ ቁጥሩ ቦሌ10/126/7/6/113255/00 የሆነ ማስወጣቱን በማወቃችን ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ በመ.ቁ 114075 በ8/5/12ዓ.ም የእግድ ትእዛዝ ለክ/ከተማው ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት ተላልፎ ጽ/ቤቱም በተራ ቁጥር 38997 ላይ ማገዱን ለፍ/ቤቱ በ14/5/12ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ አሳውቋል፡፡ ስለሆነም የተጠሪ ድርጊት የአመልካቾችን ንብረት ያለ አመልካቾች ፈቃድ የንብረት ባለቤትነት ካርታ ማውጣቱ የአመልካቾችን መብት የጣሰ ድርጊት በመሆኑ ለተጠሪ በአመልካቾች ንብረት ላይ የተሰጠው ካርታ እንዲሰረዝ እንዲሁም ንብረቱ የአመልካቾች የጋራ ሀብት ስለመሆኑ ተረጋግጦ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ አመልካቾች መብት የጠየቁበት የመሬታ ይዞታ ግምቱ ብር 312,000.00 ሳይሆን ከ10 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት በመሆኑ ፍ/ቤቱ አስፈላጊ ከሆነ ከሚመለከተው አካል የንብረት ግምት እንዲቀርብ ተደርጎ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን እንዲዘጋ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቦ ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችንም በማቅረብ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

ፍርድቤቱም ተጠሪ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በማለት ያቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ የተለያዩ ትእዛዞችን በመስጠት ምላሽ ከቀረበለት በኂላ በተጠሪ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎች መርምሮ ተጠሪ ክርክር ያስነሳውን ይዞታ የሊዝ ውልን መነሻ በማድረግ የያዝኩት ነው በማለት ክርክር ያቀረበ እና የጠቅላላ የሊዝ ውል ግምቱም ብር 25,855,127.00 በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2014 መሰረት ፍ/ቤቱ የተጠቀሰውን የዳኝነት መጠን አከራክሮ ለመወሰን የዳኝነት ስልጣን የሌለው እና ከፍ/ቤቱ ስልጣን በላይ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ተቀብሎ የማስተናገድ ስልጣን የለውም በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 231(1)(ሀ) መሰረት ክሱን ውድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቶ፤ በዚሁ መነሻም በሌሎቹ መቃወሚያዎች ላይ ብይን መስጠት አላስፈለገም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካቾች በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን ብይን እና ትእዛዝ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ የአመልካቾች መሬት የገጠር እርሻ መሬት በመሆኑ የሊዝ ህግም ሆነ የሊዝ ውል ማሻሻያ በገጠር እርሻ መሬት ላይ ተፈጻሚነት የላቸውም፡፡ ተፈጻሚነት በሌለው ሊዝ ውል ላይ የተጠቀሰ የገንዘብ መጠን ብር 25,855,127.88 የስር ፍ/ቤትን የዳኝነት ስልጣን የሚወስን ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ብይን እና ትእዛዝ እንዲሻርልን፤ ወጪና ኪሳራም እንዲከፈለን እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች የውርስ እርሻ መሬት ይገባናል ዳኝነት ጥያቄን መሰረት ተደርጎ ተጠሪ ይህን መሬት በሊዝ ያገኘሁትን ብር 25,855,127.00(ሀያ አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ አምሳ አምስት ሺህ አንድ መቶ ሀያ ሰባት ብር) ነው በመባሉ ይህን መሰረት በማድረግ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ስልጣን የለኝም ማለቱ ይህም በፌ/ከ/ፍ/ቤት መጽናቱ አግባብነት እና የፌ/ፍ/ቤቶችን ስልጣን የሚወስነው በተጠየቀው ዳኝነት አኳያ ወይስ ተጠሪ ንብረቱን ከሌላ አካል ካገኘበት ገንዘብ መጠን ልክ የሚለውን ተገቢነት ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ18/5/15ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ በ9/6/15ዓ.ም በተጻፈ ባቀረበው መልስ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ብይን እና ትእዛዝ አግባብ ነው የሚልበትን ምክንያት መዘርዘር እንዲጸና ጠይቋል፡፡

አመልካቾች በ16/6/15ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ፤ አቤቱታ ከቀረበበት ብይን እና ትእዛዝ እንዲሁም ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶች ብይን እና ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀጽ 40(3) የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነው፡፡ መሬት የማይሸጥ ፤ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው በማለት ደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆነው የገጠር እርሻ መሬት በመሆኑ ከተጠቀሰው የህገመንግስቱ ድንጋጌ አንጻር መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ በመሆኑ ብቻውን በገንዘብ ሊገመት የሚችል አይደለም፡፡

የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካቾች ባቀረቡት ክስ ለተጠሪ በአመልካቾች ንብረት ላይ የተሰጠው ካርታ እንዲሰረዝ እንዲሁም ንብረቱ የአመልካቾች የጋራ ሀብት ስለመሆኑ ተረጋግጦ እንዲወሰን ሲሉ ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ብይን የሰጠው ለክሱ መነሻ በሆነው የገጠር እርሻ መሬት ላይ ያለ ንብረትን የገንዘብ ግምት መሰረት በማድረግ ሳይሆን ተጠሪ መሬቱን በሊዝ ውል ነው ያገኘሁት በሚል ላቀረበው ክርክር በማስረጃነት ያቀረበውን የመሬት ይዞታውን የሊዝ ውል የገንዘብ ግምትን መነሻ በማድረግ ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤቱ ብይን የሚያስገነዝብ ሲሆን የሊዝ ዋጋ መሬትን ለማስተዳደር አላማ የተዘረጋ ስርአት አካል እንጂ የመሬቱ የገበያ ዋጋ ተብሎ በገንዘብ የተተመነ መሆኑን የማያሳይ በመሆኑ

የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት ለሰጠው ብይን ከላይ በተገለጸው መልኩ የሰጠውን ምክንያት ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የህግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘውም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ በ24/6/15ዓ.ም በተጻፈ ባቀረበው አቤቱታ አመልካቾች ያቀረቡትን የካርታ ይምከንልኝ/ይሰረዝልኝ የዳኝነት ጥያቄ የአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 44 እና 49 ከደነገጉት እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 220042 እና በመ.ቁ 220582 ከሰጠው የህግ ትርጉም አንጻር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አይቶ የመዳኘት ስልጣን የሌለው በመሆኑ የቀረበው ጉዳይ የሰበር ትርጉም አይፈልግም ተብሎ መዝገቡ እንዲዘጋ በማለት የጠየቀ ሲሆን ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን እንደመረመረው አመልካቾች በስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ለተጠሪ በአመልካቾች ንብረት ላይ የተሰጠው ካርታ እንዲሰረዝ እንዲሁም ንብረቱ የአመልካቾች የጋራ ሀብት ስለመሆኑ ተረጋግጦ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት የጠየቁ በመሆኑ ይህም ከካርታ ይሰረዝልኝ ጥያቄ በተጨማሪ የንብረት ባለቤትነት በፍ/ቤት ውሳኔ እንዲረጋገጥ ዳኝነት የተጠየቀበት በመሆኑ እና የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለው በመሆኑ በተጠሪ የቀረበውን አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

ስለሆነም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካቾች ባቀረቡት ክስ ለተጠሪ በአመልካቾች ንብረት ላይ የተሰጠው ካርታ እንዲሰረዝ እንዲሁም ንብረቱ የአመልካቾች የጋራ ሀብት ስለመሆኑ ተረጋግጦ እንዲወሰን ሲሉ ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ተቀብሎ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን እና በዚሁ ብይን ላይ የቀረበውን ይግባኝ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሰረዝ የሰጠው ትእዛዝ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 40(3) ድንጋጌ አንጻር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው ሆኖ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያገኘው በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 131795 በ07/10/14ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 294480 በ27/12/14ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካቾች በተጠሪ ላይ በ07/9/14ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት ክስ ለተጠሪ በአመልካቾች ንብረት ላይ የተሰጠው ካርታ እንዲሰረዝ እንዲሁም ንብረቱ የአመልካቾች የጋራ ሀብት ስለመሆኑ ተረጋግጦ እንዲወሰን ሲሉ ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ተቀብሎ የማየት ስልጣኑ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው በማለት ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት ወስኗል፡፡
3. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋውን የመ.ቁ 131795 የሆነውን መዝገብ አንቀሳቅሶ አመልካቾች በተጠሪ ላይ ያቀረቡትን ክስ ፍ/ቤቱ ተቀብሎ የማየት ስልጣን የለውም ሲል ተጠሪ ካቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውጪ ያሉትን ሌሎቹን የተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ

መቃወሚያዎች መርምሮ በጉዳዩ ላይ የመሰለውን ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡

4. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
6. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም